የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA
አዲስ አበባ/ADDIS ABABA

# "የህጋዊ ገንዘቦች ጥበቃ መመሪያ (ማሻሻያ) ቁጥር ከማዳ 02/2021"

የባንክ ኖቶች በክምችት እንዳይያዙ የተጣለውን ገደብ ይበልጥ በማሳነስ ህገወጥ ተግባራትን ማዳከም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም፣የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ (እንደተሻሻለ) አዋጅ ቁጥር 591/2008 አንቀጽ 27(2) በተሰጠው ስልጣን መሠረት የአገሪቱን ህጋዊ የገንዘብ ኖቶች ለመጠበቅ ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "ህጋዊ የብር ኖቶችን ለመጠበቅ የወጣ (ማሻሻያ) መመሪያ ቁጥር ከማዳ/02/2021" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ማሻሻያ**

   ይህ የህጋዊ ገንዘቦች ጥበቃ መመሪያ ቁጥር ከማዳ/1/02/2020 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

   1. የዚህ መመሪያ አንቀፅ 3.7 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 3.7 ተተክቷል:

      "3.7 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 3.6 የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ ተፈጥሮአዊ ሰው የሆነ በአንድ ጊዜ እስከ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) መያዝ የሚችል እና በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል እስከ ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) መያዝ ይችላል"

   2. የዚህን መመሪያ አንቀጽ 4.4 ተከትሎ አዲስ አንቀጽ 4.5 ተጨምሯል:

      "4.5 አንቀፅ 3.7ን በሚጥስ መልኩ ከጣሪያው በላይ በክምችት ተይዘው የተገኙ የባንክ ኖቶች በአዋጅ ቁጥር 591/2008 ንዑስ አንቀፅ 26(1)(መ) መሠረት የሚወረሱ ይሆናል"

   3. የዚህን መመሪያ አንቀፅ 4 ተከትሎ አዲስ አንቀፅ 5 የተጨመረ ሲሆን ነባሩ አንቀፅ 5 አንቀፅ 6 ተብሎ ተሸጋሽጓል፡፡



አድራሻ: ሱዳን ጎዳና: Address: Sudan Street | ፖ.ሣ.ቁ.: P. O. Box: 5550/2048 | ፋክስ: Fax No.: +251-11-551-4588 | ስልክ ቁጥር: Tel. No.: +251-11-551-7430 | Website: www.http://nbe.gov.et SWIFTCODE - NBETETAA

"5. <u>መሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ መመሪያ ተፈፃሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሶስት ተከታታይ ቀናት ውስጥ ማንኛውም ከተቀመጠው ገደብ በላይ ተከማችቶ የተያዘ የባንክ ኖት ከላይ በአንቀጽ 3.7 ወደ ተቀመጠው ገደብ መውረድ አለበት፡፡

3. <u>ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን</u>

ይህ መመሪያ ከመጋቢት 1 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ይናገር ደሴ (ዶ/ር)
ገዥ